**የብስኩት ማምረቻ ፕሮጀክት መገለጫ(project profile on biscuit production)**





ብስኩት ጣፋጭ፣ደረቅና ጠፍጣፋ ወይም የተለያ ቅርጽ ያለው ሆኖ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ነው፡፡ አብዛኛው ጊዜ ልጆችና ወጣቶች ከሚመገቧቸው የምግብ ዝርዝር ውስጥ ይመደባል፡፡ በውስጡ ለጤና ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ የምግብ ንጥረ ነገሮችን በመያዝ ይዘጋጃል፡፡

ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ በአብዛኛው የልጆች እና የወጣቶች ቁጥር ከፍተኛውን ስለሚይዝ ምርቱን የሚጠቀሙ የህብረትሰብ ክፍሎች በተመሳሳይ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በአገሪቱ ውስጥ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ የሚያደርግ የብስኩት ፋብሪካ በበቂ መጠን አለመኖሩ በዘርፉ ላይ የገበያ ክፍተት መኖሩን ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መረጃ የብስኩት ምርት ለማምረት 113 ድርጅቶች ብስኩትና ተያያዥ ምርቶች ለማምረት መመዝገባቸውን ያስረዳል፡፡ ከተመዘገቡት ውስጥ 74 ፐርሰንት የሚሆኑት በቅድመ ትግበራ ደረጃ የሚገኙ፣ 10 ፐርሰንት የሚሆኑት በትግበራ ላይ ሲሆኑ የተቀሩት 16 ፐርሰንት ያህሉ ደግሞ በማምረት ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ በአገሪቱ ውስጥ በስራ ላይ የሚገኙት ከ18 በላይ የብስኩት ፋብሪካዎች በስራ ላይ ቢሆኑም የአገሪቱን የገበያ ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ ማሟላት የሚችሉ ግን አይደሉም፡፡ በመሆኑም ባለፉት አስር አመታት በተከታታይ በአማካይ 555,420 ኪሎ ግራም ጣፋጭ ብስኩት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ገብቷል፡፡ ወደ ፊትም በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ቁጥሩ እያደር በመጨመር በ2024 ዓ.ም 1,494,874 ኪሎ ግራም ብስኩት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ እንደሚገባ ይገመታል፡፡

የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የገቢ መጠን ማደግ፣ የአመጋገብ ስርዓት መሻሻል ወደ ፊት የብስኩት ፍላጎት ለመጨመር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት የአገር ውስጥ የብስኩት አቅርቦት በአማካይ በአመት 994,032 ኩንታል ሲሆን እድገቱ በአመት በ2.5 እንደሚጨምር ይታሰባል፡፡ አንድ ሰው በአማካይ 1.2 ኪሎ ግራም ብስኩት በአመት ቢመገብ ከህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ተያይዞ በ2024 ዓ.ም አገሪቱ 184,643,510 ኪሎ ግራም የብስኩት ፍላጎት መጠን ይኖራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ወቅት እንኳን የአገር ውስጥ ብስኩት ምርት እና ከውጭ የሚገባው አቅርቦት መጠን በአንድ ላይ ተደምሮ

አገር ውስጥ ፍላጎትን ማሟላት ባለመቻሉ 45,066.130 ኪሎ ግራም የፍላጎት ክፍተት እንዳለ የፕሮጀክት ጥናት መረጃ ያመለክታል፡፡ በሚቀጥሉት አስር አመታትም ቁጥሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊጨምር እንደሚችል ይታሰባል፡፡

አዲስ አበባ የአገሪቱ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የንግድ ፣የትምህርት እና የቴክኖሎጂ ማዕከል መሆኗ የብስኩት ማምረቻ ፋብሪካ ላይ ኢንቨስት ቢያደርጉ፡-

- ✓ ከቀረጥ ነጻ የማበረታቻ ማሽንና የማምረቻ ማሽን ጠቅላላ ዋጋ 15% መለዋወጫ ከቀረጥ ነጻ ይፈቀዳል፡፡
- ✓ ኢንቨስተሮች ለሚያመርቱንት ጥሬ ዕቃ ወይም የግንባታ ቁሳቁስና ከአገር ውስጥ ገበያ ሲገዙ የቀረጥ ነጻ ተመላሽ ይደግላቸዋል፡፡
- ✓ ፕሮጀክቱ ምርቱን ማምረት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ የ3 ዓመት የገቢ ግብር እፎይታ ጊዜ ይኖረዋል፡፡
- ✓ ለስራው አገልግሎት የሚውል አንድ ሽፍን ደሊቨሪ ቫን መኪና እና አንድ የጭነት መኪና ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ይፈቀዳል፡፡
- ✓ አልሚዎች በኢንዱስትሪያል ፓርኮች ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ እና ምርቱን ወደ ውጭ የሚልኩ ከሆነ ተጨማሪ የግብር እፎይታ ጊዜ እና የገቢ ግብር ማበረታቻ ያገኛሉ፡፡

የፋይናንሽያል ሁኔታ፡-

- ➢ አጠቃላይ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገው ካፒታል 279,199,500 ብር ነው፡፡
- ➢ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲደረግ 70% ካፒታል በብድር የሚገኝ ሲሆን 30% የሚሆነው ደግሞ ከባለቤቱ ይሸፈናል፡፡ ብድሩ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሚገኝ ከሆነ ለ10 ተከታታይ ዓመታት 11.5% ዓመታዊ ወለድ ሊታሰብ ይችላል፡፡
- ➢ የፕሮጀክቱ የቆይታ ጊዜ እርዝማኔ አስር ዓመት ይሆናል፡፡
- ➢ ፕሮጀክቱ ያወጣውን ካፒታል ሙሉ ለሙሉ ለመመለስ የ5 ዓመት ቆይታ ጊዜ ብቻ ይፈጅበታል፡፡
- ➢ ብሬክ ኢቪን ፖይንት ሽያጭ 234,992,481 ብር ስለሆነ ለማትረፍ የግድ ሽያጩ ከዚህ በላይ መሆን አለበት፡፡
- ➢ በአራተኛ ዓመት ፕሮጀክቱ የተጣራ ትርፍ 73,303,000 ብር ሲሆን በአስረኛው ዓመት ላይ 92,624,000 የተጣራ ትርፍ ያገኛል፡፡
- ➢ የባለቤቱ ተመላሽ ካፒታል በፕሮጀክቱ ዓመታዊ ትርፍ ሲሰላ 45% ያህል ነው፡፡ በተመሳሳይ ጥቅል ተመላሽ ካፒታሉ የጠቅላላ የኢንቨስትመንቱን 13.6% ያህል ነው፡፡

በመሆኑም አዲስ አበባ ከተማ ፈጣን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ያለባት ፣ በቂ የመሰረተ ልማት አውታር የተዘረጋባት ፣ ሰላም የሰፈነባት ከተማ በመሆኗ ከላይ የጠቀሱትን መረጃዎች በማየት የብስኩት ማምረቻ ፋብሪካ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ማቋቋም አዋጭ እና ጠቀሜታው እጅግ የጎላ መሆኑን ልንጠቁምዎ እንወዳለን፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ኮሚሽን